፲፱ ፡ ወይማርሩ ፡ ለርእሶሙ ፡ መሠረተ ፡ ሠናየ ፡ ለዘይመጽእ ፡ ዓለም ።

ለሚመጣው ፡ ዓለም ፡ ለራሳቸው ፡ በጎ ፡ ቢጋርን ፡ ይበግሩ ፡ ዘንድ ፡ (እስ ፡)በጎ ፡ ተስፋን፡ ይይዙ፡ዘንድ

ከመ ፡ ይርከቡ ፡ ሕይወተ ፡ ዘበአማን ፡(ማቴ ፡፲ ፡፰ ።)

የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ መንግሥት ፡ ለማይን ፡ ለመውረስ ።

፳ ፡ ኦ ጢሞቴዎስ ፡ ዕቀብ ፡ ማኅፀንተከ ፡ (፪፡ ጢሞ ፡፩ ፡፲፬ ።)

ጢሞቴዎስ ፡ አደራህን ፤ ጠብቅ ። እንድም ፡ አደራህን ፡ ጠብቅ ።

ተግኀሦሙ ፡ ለርኩሳን ፡ እለ ፡ ያመጽኡ ፡ ነገረ ፡ ከንቶ ፡ (፩፡ ጢሞ ፡፬ ፡፯ ።)

ከንቱ ፡ ነገርን ፡ የሚያመጡ ፡ ድል ፡ የቶነው ፡ ሰዎችን ፡ ተለያቸው ።

ወያሌልልዋ ፡ ለጽድቅ ፡ በሐሰት ።

ጽድቅን ፡ በኃጢአት ፤ እውነትን ፡ በሐሰት፤ እምልኮትን ፡ በክህደት ፡ ወንጌልን ፡ በኦሪት ፡ የሚለውጡ
ትን ፡ ተለያቸው ።

፳፩ ፡ እለሙ ፡ እሉ ፡ ስሕቱ ፡ እምተዐቅቦ ፡ ሃይማኖት ።

እሊህ ፡ ስምና ፡ ከሚገኘው ፡ ተለሉ ፡ ወየተቆልና ።

ጸጋ ፡ ምስሌከ ፡(ም ፡፭ ፡፳ ፡፱ ጢሞ ፡፬ ፡፲፰ ።)

ጸጋ ፡ አድሮብህ ፡ ይኑር ።

አሜን ።　　　　　　　　በእውነት ።

ተፈጸመ ፡ መልእክት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀበ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ወተጽሕፈ ፡ በእቴና ፡ ወተፈነወ ፡ በእደ ፡ ቲቶ ።

በእቴና ፡ የተጻፈ ፡ በቲቶ ፡ እጅ ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ የተላከ ፡ መጀመሪያ ፡ ክታብ ፡ ደረሰ ፡ ተፈጸመ ።

ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ።

እንዲሆም ፡ [illegible] ገባው ።

www.ethiopianorthodox.org